# የትምህርት ዓመት 2020-2021 የምዝገባ መመሪያ እና ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

በክልላችን የCOVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ እንዲረዳ፣ ሁሉም የDCPS ትምህርት ቤት ህንፃዎች በአሁኑ ወቅት ዝግ የሆኑና የርቀት ትምህርትም እየተሰጠ ይገኛል። ስለ ምዝገባ ሂደቶች እና የማብቂያ የጊዜ ገደብን በተመለከተ የተሰጠውን ይፋዊ አዲስና ማሻሻያዎችን፣ እባክዎን ከዚህ በታች ያግኙ። እነዚህ መመሪያዎች እስከ የትምህርት ዓመት ማብቂያው ቀን፣ አርብ ግንቦት 21፣ 2012 ዓ.ም (May 29, 2020) ድረስ በስራ ላይ ይውላል።

የሚከተለው ወቅታዊ ሆኖ ከሰኞ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም (April 27, 2020) ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል።

**DCPS** ለቤተሰቦቻችን ምዝገባን በመጀመሩ እና አዲስ ተማሪዎችን ወደ ማህበረሰባችን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት በመቻሉ ደስታ ተሰምቶታል**!** ከ51,000 በላይ ተማሪዎችን ለማገልገል በመቻላችን ኩራት ይሰማናል፤ እንዲሁም ከቤተሰብዎ ጋር በመሆን፣ የ2020-2021 (SY20-21) የትምህርት ዓመትን በማስጀመራችን ደስታ ተሰምቶናል።

በSY20-21 የምዝገባ ሂደት እና የማብቂያ የቀን ገደቦች ላይ የተደረጉ ቁልፍ የሆኑ አዲስና ማሻሻያዎች:

- ለSY20-21 ምዝገባ፣ በኤሌክትሮኒክ ማስገቢያ ሂደት ከሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ጀምሮ መገኘት ይችላል። የምዝገባ ጥራዙን (**packet**) እዚህ ያግኙ።
- በMy School DC፣ የተዛመዱበትን ቦታ ለመውሰድ የሚጠየቁበትን የማብቂያ የጊዜ ገደብ አራዝሟል። ቤተሰቦች፣ እስከ **5:00 pm**፤ ሰኞ፣ ሰኔ **8** (**June 15**) ድረስ መመዝገብ እና ቦታቸውን ለመውሰድ መጠየቅ አለባቸው።

## ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች FAQs

**1.** ይህ የት/ቤት መዘጋት፣ በ'**My School DC**' ሎተሪ የምዝገባ የማብቂያ የጊዜ ገደብ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል**?**
ለSY20-21፣ በሎተሪ-መዛመጃ ቦታ ለመመዝገብ እና ቦታውን ለመውሰድ የመጠየቂያው የጊዜ ገደብ ማብቂያ እስከ **5:00 pm**፤ ሰኞ፣ ሰኔ **8** (**June 15**) ድረስ ተራዝሟል።

**2.** እስከ የትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸው የተነሣ፣ ተማሪዎቼ ያገኙት የተዛመደ ቦታቸውን ያጣሉ**?**
ሁሉም መዛመዶች እስከ 5:00 pm፣ ሰኞ ሰኔ 8 (June 15) ድረስ ዋስትና አላቸው። ቤተሰቦች እስከዚህ ጊዜ ድረስ ለመመዝገብ እና ቦታቸውን ለመውሰድ ይችላሉ። ለማስታወስ ያህል፤ ሁሉም ቤተሰቦች ከK እስከ 12 ክፍሎች፣ ምንጊዜም ቢሆን በክልል ወሰን ትምህርት ቤታቸው (in-boundary school) ውስጥ፣ ቦታ የማግኘት ዋስትና አላቸው።

**3.** ተማሪዬ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ከሰኞ ሰኔ **8** (**June 15**) በፊት ከተጠራ፣ ለመመዝገብና የተሰጠውን ቦታ ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ ይኖረዋል**?**
ከሰኞ ሰኔ 8 (June 15) ቀን በፊት፣ አምስት የሥራ ቀናት በላይ ቀደም ብሎ ቦታው የተሰጠው ማንኛውም ተማሪ፣ ለመመዝገብ እና ቦታውን ለመውሰድ የሚኖረው ጊዜ እስከእዚያ እስከ ሰኞ፣ ሰኔ 8 (June 15) ድረስ ይሆናል።

**4.** ለ**SY20-21**፣ ተማሪዬን መቼ እና እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ**?**
DCPS የምዝገባ ጊዜን ለቤተሰቦች አስጀምሮ፣ አዲስ ተማሪዎችን ወደ ማህበረሰባችን እንኳን ደህና መጣችሁ ሲል ደስታ ይሰማዋል! ለSY20-21 ምዝገባ ማስገቢያነት የሚያገለግል፣ የኤሌክትሮኒክ የማስገቢያ ሂደት ከዛሬ፣ ሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ጀምሮ ዝግጁ ይሆናል። ይህን ሂደት ለማጠናቀቅ፣ ወላጆች የኢሜል አድራሻ ያስፈልጋቸዋል። ኮምፒውተር፣ ስማርትፎን (smartphone)፣ ወይም ሌላ የሞባይል ዲቫይስ በመጠቀም፣ የምዝገባ ጥራዙን (**packet**) እዚህ ያግኙ። ምዝገባውን ለማጠናቀቅ የሚከተሉትን የእርምጃ ደረጃዎች ይከተሉ:

1. ተገቢ የሆነውን ሊንክ (**link**) በመምረጥ፤ የምዝገባ ጥራዙን (packet) ማጠናቀቅ።
   — የምዝገባ ቅጾች በስድስት ቋንቋዎች መገኘት ይችላል (እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ ቬትናም፣ ፈረንሳይኛ፣ ቻይኒኛ)። እያንዳንዱ ቋንቋ ልዩ የሆነ ማገናኛ/ሊንክ (link) አለው።
2. የደብዳቤውን የመጀመሪያ ገጽ ሙሉ በሙሉ ያንብቡ።
   — የደብዳቤው የመጀመሪያ ገጽ (cover letter)፣ ምዝገባውን እንዴት መሙላት እንደሚችሉ እና የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝዎን (packet) ለማስገባት ምን ዓይነት ሰነዶች እንደሚያስፈልግዎት፤ ጠቃሚ የሆነ መረጃዎችን አካቶ ይዟል።

3. ሁሉንም የተጠየቁትን፤ የሚፈለጉ እና የሚመለከተውን መረጃዎች ይሙሉ።
   — አንብበው ማጠናቀቅ ያለብዎት፣ 7 (ሰባት) ገጾች አሉ።
   — አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች በሙሉ፣ ከከብ (አስተሬክስ) ምልክት (*) ተደርጎባቸው ተለይተዋል።
   — በቅጹ ላይ የሚገኘውን ከሞሉ በኋላ፤ እንደገና ትክክለኛነቱን ደግመው ተመልከተው ሙሉ በሙሉ ካልጨረሱ በስተቀር፣ በቅጹ ላይ የሚገኘውን "*Signature Here*"የሚለውን አማራጭ አይምረጡ። ከመፈረምዎ በፊት ሁሉንም 7 (ሰባት) ገጾች ተመልክተው እና አጠናቀው መጨረስ አለብዎት።
   — ጥራዙን (packet) አጠናቆ ለመጨረስ ጊዜ ከሌለዎት፣ ከታች ከስክሪኑ (screen) እግርጌ በሚገኘው የጽሁፍ ሰሌዳ (banner) ላይ የሚገኘውን "***Save and Continue Later***" የሚለውን አማራጭ ይምረጡ። ይህም በSeamlessDocs ውስጥ፣ አካውንት እንዲፈጥሩ ያደርግዎታል።
4. አንደኛዉኑ፣ ሁሉንም ገጾች ካጠናቀቁ በኋላ፣ ከታች በስክሪኑ (screen) የጽሁፍ ሰሌዳ (banner) ላይ የሚገኘውን፣ "***Submit and Sign***" የሚለውን ቁልፍ (**button**) መምረጥ።
5. የሚመለከተውን አባሪዎች (**attachments**) እንዲጫኑ (**upload** እንዲያደርጉ) ይጠየቃሉ።
   — አዲስ ተማሪዎች፣ አንድ የዕድሜ ማረጋገጫ ሰነድ ማስገባት አለባቸው። ተቀባይነት ያላቸው የዕድሜ ማረጋገጫ ሰነዶች፤ በምሳሌነት ከተካተቱት ውስጥ – የልደት የምስክር ወረቀት፣ የሆስፒታል መዝገቦች፣ የቀድሞ ትምህርት ቤት ሰነዶች፣ ፓስፖርት(passport) ወይም የጥምቀት የምስክር ወረቀት ናቸው። ይህ ዝርዝር እዚህ ሊገኝ ይችላል።
   — ሁሉም የዲሲ ነዋሪዎች፣ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ተቀባይነት ያለው የዲሲ የነዋሪነት ሰነዶች [እዚህ](#) ሊገኙ ይችላሉ።
   — ጥራዙን (packet) ሞልተው ለማጠናቀቅ ከመጀመርዎ በፊት፣ ሁሉንም ሰነዶችዎን ለመጫን (upload) ለማድረግ እንዲያሰናዱ እናበረታታዎታለን።
   — ምስሎችን (pictures) ጨምሮ፤ የተለያየ የይዘት አቀራረቦች (formats) ያላቸው ሰነዶች ሊጫኑ (upload ሊደረጉ) ይችላሉ።
6. የኤሌክትሮኒክ ፊርማዎን ለመፍጠር የሚያግዘውን ትዕዛዝ በመከተል እና በጥራዙ ላይ በሚፈለገው በ6 (ስድስት) ቦታዎች ላይ ፊርማዎን ያኑሩ።
7. አንድ ጊዜ፣ ፊርማዎን በሚፈለጉት ቅጾች ላይ ካስገቡ በኋላ፣ "***Finalize and Submit***" የሚለውን ይምረጡ።
8. ሌላ ማን ይህን ሰነድ ሊፈርም እንደሚያስፈልገው (*Who Else Needs to Sign this Document)*፣ ይጠየቃሉ፤ ከዚያም በኋላ፣ ወደታች ከሚዘረዘረው (drop-down) ምርጫ፣ ምዝገባውን የሚሞሉበትን ትምህርት ቤት ይምረጡና፣ "***Continue***" የሚለውን ተጭነው፣ የምዝገባ ጥራዙን (packet) ያስገቡ።

አንዴ ካስገቡት በኋላ፣ ያስገቡት ጥራዝ (packet) ቅጂ/ኮፒ ይደርስዎታል። ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤቱ ያስገቡትን ይመለከታል፣ እንደአስፈላጊነቱ ከእርስዎ ጋር ክትትል ያደርጋል፣ እና ጥራዙን (packet) ይፈርማል፤ ይህም ምዝገባው መጠናቀቁን ያመላክታል። ከዚህ በኋላ በትምህርት ቤቱ የተፈረመበት ሌላ ቅጂ/ኮፒ ያገኛሉ። ያስገቡትን አባሪዎች (*attachments*) ማግኘት ከፈለጉ፣ [ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ።](#) ምዝገባዎ እስከመጨረሻ እንደተጠናቀቀ የሚቆጠረው፣ ቅጽዎትን ትምህርት ቤቱ በህጋዊነት ከፈረመ እና ይህ መከናወኑን የሚያረጋግጥ ኢሜል ሲደርስዎ ነው።

5. **በኤሌክትሮኒክ ማስገቢያ ሂደቱ፣ በሞባይል ለመጠቀም ቀላል የሆነ (mobile-friendly) ነው?**
   አዎን። ለSY20-21 ምዝገባ፣ የኤሌክትሮኒክ ማስገቢያ ሂደት በሞባይል ለመጠቀም ቀላል የሆነ (mobile-friendly) ስለሆነእና ከስማርትፎን (smartphone) ወይም ሌላ የሞባይል ዲቫይስ ለመጠቀም ይቻላል። ሰነዶችን (documents) ለመጫን (upload ለማድረግ) ከፈለጉ፣ እነዚህን ሰነዶች (documents) ወይም ምስሎች (pictures) በሞባይል ዲቫይስዎ ውስጥ መገኘታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ።

6. **የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝን (packet)፣ በኤሌክትሮኒክ ለማስገባት እርዳታ ቢያስፈልገኝስ ምን ይሆናል?**
   ምዝገባውን ወደ ትምህርት ቤትዎ ለማስገባት በማንኛውም መንገድ እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን [ትምህርት ቤትዎን ያነገግሩ](#) ወይም [enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov) ኢሜል ያድርጉ።

7. **የSY20-21 የምዝገባ ጥራዙን (packet)፣ ለማስገባት የሚያስፈልጉት እንደ የሞባይል ዲቫይስ፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ላፕቶፕ (laptop)፤ ከሌለኝ ምን ይሆናል?** ሌላ አማራጭ የሆነ የምዝገባ ማስገቢያ ሂደት ካስፈለገዎት፣ እባክዎን [ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ](#) ወይም [enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov) ኢሜል ያድርጉ።

8. **የDCPSን የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet) እና ሌሎች ከምዝገባ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቅጾች ከየት አገኛለሁ?**

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

የSY20-21፣ የDCPS የምዝገባ ጥራዝ (Packet) እና ሌሎች ከምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅጾች፣ [እዚህ](#) ይገኛሉ።

**9.** ቤተሰቦች የዲሲ ነዋሪነታቸውን የሚያረጋግጡበት ሁኔታዎችን በተመለከተ፣ የተደረጉ ለውጦች አሉ**?**
በSY20-21 በሚቀርቡ መስፈርቶች ላይ፣ ለቤተሰቦች ምንም የተደረገ ለውጥ የለም፣ ነገር ግን አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማስገባት አማራጭ ዘዴዎች ቀርበዋል። አሁንም ቢሆን፣ ሁሉም ቤተሰቦች – የDCPS የምዝገባ ጥራዝ (packet) መሙላት፣ የዲሲ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ፣ እና ሁሉንም ሰነዶች ወደ ትምህርት ቤታቸው ማስገባት አለባቸው። ተቀባይነት ያላቸው የዲሲ ነዋሪነት የሰነድ ማስረጃ [እዚህ](#) ይገኛል።

የትምህርት ቤት ህንፃዎች እስከ የትምህርት ዓመቱ ማብቂያ ድረስ በመዘጋታቸው ምክንያት፣ ሌላ ማስታወቂያ እስከሚሰጥ ድረስ ቤተሰቦች የምዝገባ ወረቀቶችን ወደ ትምህርት ቤቶች በግንባር ቀርበው ማስገባት አይችሉም። ቤተሰቦችንና ትምህርት ቤቶችን ለመርዳት፣ ሁሉንም የምዝገባ ሰነዶችን፤ የዲሲ ነዋሪነት ወረቀቶችን እና የኤሌክትሮኒክ ፊርማ (e-signature) መስጠት የመቻል አማራጭነት መኖርን ጨምሮ፣ DCPS ተገቢ የሆነ የኦንላይን ማስገቢያን ለቤተሰቦች አዘጋጅቷል። አሁን፣ ይህ አማራጭ ከሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ጀምሮ አገልግሎት ላይ ይውላል።

**10.** በ**SY20-21**፣ ከጤና ጋር ግንኙነት ያላቸው የምዝገባ መስፈርቶች ላይ የተደረጉ ለውጦች አሉ**?**
ከዚህ በላይ የተገለጸው የምዝገባ ሂደት ለውጦች እንዳሉ ሆኖ፣ በአሁኑ ወቅት OSSE፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፣ የአለም ዓቀፍ የጤና ሰርተፊኬት (Universal Health Certificates) እና የአፍ ጤና እገዛዎች (Oral Health Assessments) መረጃዎችን በምዝገባ ወቅት ሳይሆን፣ በSY20-21 መጀመሪያ ላይ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። ለማስታወስ ያህል፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ለመማር፣ የክትባት (immunizations) ማረጋገጫዎቻቸው ወቅታዊነቱን የጠበቀ መሆን አለበት።

**11.** ስለምዝገባው ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉኝ፣ ማንን ነው የማነጋግረው**?**
ጥያቄዎች ካለዎት፣ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች እንዲከተሉ እናበረታታለን:

- የ[DCPS የምዝገባ ድህረ-ገጽ](#)ን ይጎብኙ።
- ከምዝገባ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥያቄዎችዎን ይዘው፣ በቀጥታ [ትምህርት ቤት](#)ዎን ያነጋግሩ።
- የምዝገባ ቡድኑን በenroll@k12.dc.gov ወይም በ(202) 478-5738 ያነጋግሩ።
- ከሎተሪ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን ብቻ ለመጠየቅ፣ የ'My School DC'ን በ(202) 888-6336 ወይም በinfo.myschooldc@dc.gov ያነጋግሩ።